

የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ

የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ

ሰኔ/2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

ክፍል አንድ፡- 1

1.1 *መግቢያ* 1

1.2 የእቅዱ መነሻ ሁኔታዎች፣ 2

1.2.1 የትብብር መድረኩ ስትራቴጂክ ዕቅድ 2

1.2.2 የ2016 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም 2

1.3 *ራዕይ፣ተልዕኮና ዕሴቶች* 3

1.3.1 *ራዕይ* 3

1.3.2 *ተልዕኮ* 3

1.3.3 *ዕሴቶች* 3

1.4 የትብብር መድረኩ የትኩረት አቅጣጫዎች 3

ክፍል ሁለት፡- 4

2. የበጀት ዓመቱ ዕቅድ ጥቅል ግብና ዓላማ 4

2.1 ጥቅል ግብ 4

2.2 ጥቅል ዓላማ 5

2.3 ዝርዝር ዓላማዎች 5

2.4 በመደበኛ በጀት የሚከናወኑ የፕሮግራም ግቦችና ዝርዝር ተግባራት 6

2.4.1 የልምድ ልውውጥና እውቀት ሽግግርን በተመለከተ 6

2.4.2 የአቅም ግንባታ ስልጠናን በተመለከተ፣ 10

2.4.3 የሃብት ማፈላለግና ኔትወርኪንግ ስራዎችን በተመለከተ 12

2.4.4 የኮሙኒኬሽን ስራዎች በተመለከተ 13

2.4.5 የፕሮግራምና የፕሮጀክት ስራዎች የክትትልና ግምገማ ተግባራት 17

2.5 በፕሮጀክት በጀት የሚከናወኑ የፕሮግራም ግቦችና ዝርዝር ተግባራት 18

2.6 የአስተዳደርና ፋይናንስ ስራዎች 19

ክፍል ሶስት፡- 22

3. የበጀት ዕቅድ፤ መልካም አጋጣሚዎችና ታሳቢ ስጋቶች፤ 22

3.1 የበጀት ዕቅድ 22

3.2 እቅዱን በመተግበር ሂደት ያሉ መልካም አጋጣሚዎች እና ታሳቢ ስጋቶች 23

ክፍል አራት፡- 24

4. የዕቅድ ማስፈጸሚያ ስልቶች፤ 24

4.1. የክትትል፣ግምገማ፤ ግብረ መልስና ሪፖርት ሥርዓት 24
4.1.1 የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት 24
4.1.2 የግምገማ፤ ሪፖርትና ግብረ-መልስ ሥርዓት 26
5. ማጠቃለያ 27

ክፍል አንድ፡-

1.1 መግቢያ

የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት በከተሞች የሚታየውን ያልተመጣጠነ ዕድገት ችግር ለመቅረፍ ከተሞች የዕርስ በርስ ግንኙነታቸውን በማጠናከር፣ ከሌሎች መልካም ተሞክሮ ካላቸው የአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አገር ከተሞች የልምድ ልውውጥ በማድረግ ጠቃሚ አማራጮችንና ልምዶችን በመውሰድና በመቀመር በአባል ከተሞች የማስፋፋት ስራ እንዲሁም በፖሊሲና በከተማ አመራር ጉዳዮች ላይ የራሱን ድርሻ ለመወጣት በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህን የተቀመጡ አላማዎች ለማሳካት የከተሞችን ፍላጎት በማካተት፣ የስራ አስፈጻሚ ቦርድና የጠቅላላ ጉባኤውን አቅጣጫና የሴክተሩን ስትራተጂክ ጉዳዮችና ዕቅዶች እንዲሁም የ2016 የትብብር መድረኩን አመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም ግምት ውስጥ ያስገባ የ2017 በጀት አመት ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡

በዚህም መሰረት በ2016 በጀት ዓመት ከተሞች ዘላቂ ልማት የሰፈነባቸው፣ለነዋሪዎቻቸው ምቹ እንዲሆኑ እና መልካም አስተዳደር የሰፈነባቸው እንዲሆኑ ለማድረግ የተለያዩ ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ የበጀት ዓመቱን እቅድ አፈጻጸም መነሻ በማድረግም በአፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችንና ድክመቶችን ገምግሟል፡፡
በ2017 በጀት ዓመትም በቀጣይ የአፈጻጸም ስልቶችና የትኩረት አቅጣጫዎች አንጻር አሁን ያሉ ችግሮችን በመፍታትና መልካም ጅምሮችን አጠናክሮ በማስቀጠል፤ የአባል ከተሞችን አመራርና ፈጻሚዎችን የዕውቀትና የክህሎት ክፍተታቸውን በመሙላት፤ብቃታቸውን በማሳደግና ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው ምቹ የልማትና የመልካም አስተዳደር ማዕከላት ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎችን ለማከናወን ታቅዷል፡፡

ይህ ዕቅድ በትብብር መድረኩ ስር የተዋቀሩትን የስራ ክፍሎች ማለትም የአቅም ግንባታና እውቀት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት፣ የኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት፤ የአስተዳደርና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬትንና የዕቅድ ዝግጅት፤ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ዝርዝር ዕቅድ በማካተት በአራት ክፍሎች ተደራጅቶ ቀርቧል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል መግቢያ፤ የዕቅዱን መነሻ ሁኔታዎች፤ የድርጅቱን ራዕይ፤ ተልዕኮ፤እሴቶችና የትኩረት አቅጣጫዎች የሚተነትን ሲሆን በክፍል ሁለት የዕቅዱን ጥቅል ግብ፤ዓላማ እንዲሁም በመደበኛና በፕሮጀክት በጀት የሚከናወኑ ግቦችና ተግባራት

የተቀመጡበት ነው። ክፍል ሶስት የዕቅዱን ጥቅል በጀት፤መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶች ያካተተ ሲሆን በክፍል አራት ደግሞ የክትትል፣ ግምገማ፤ ግብረ-መልስና ሪፖርት ሥርዓት እንዲሁም ማጠቃለያን የያዘ ነው።

1.2 የእቅዱ መነሻ ሁኔታዎች፣

የዕቅዱ መነሻ የሆኑት በዋናነት የከተማ ልማት ሃገራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች፣ የትብብር መድረኩ የአምስት ዓመት (2015-2019) ስትራቴጂክ ዕቅድ እና የ2016 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ናቸው።

1.2.1 የትብብር መድረኩ ስትራቴጂክ ዕቅድ

ትብብር መድረኩ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴና የጠቅላላ ጉባኤውን አቅጣጫና የሴክተሩን ስትራቴጂክ ጉዳዮች ታሳቢ በማድረግ የአምስት ዓመት (2015-2019) ስትራቴጂክ ዕቅድ አዘጋጅቷል። በመሆኑም የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ ለማዘጋጀት እንደመነሻ ተወስዷል።

1.2.2 የ2016 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም

የትብብር መድረኩ በ2016 በጀት ዓመት ካከናወናቸው ተግባራት መካከል አባል ከተሞችን መሰረት ያደረጉ 3 ስልጠናዎችና 3 አውደጥናቶች በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ተዘጋጅተው አባል ከተሞች እንዲማሩባቸውና ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲገቡ ተደርጓል። በተመሳሳይ 26 የአባል ከተሞች ከንቲባዎችና አመራሮች እንዲሁም የትብብር መድረኩ ማኔጅመንት አባላት በውጭ አገር ትምህርታዊ ጉዞዎች ልምድና ተሞክሮ እንዲቀስሙ ተደርጓል። በበጀት አመቱ የትብብር መድረኩን የአባላት ቁጥር ለመጨመር በተደረገው ጥረት 17 አዳዲስ ከተሞች በአባልነት እንዲቀላቀሉ ተደርጓል። ከተሞች በትብብር መድረኩ በተመቻቹ የተለያዩ መድረኮች ያገኙዋቸውን ልምዶችና ተሞክሮዎች ምንያህል ተግባራዊ እያደረጉ እንዳሉና በከተሞች ያሉ የተሻሉ አፈጻጸሞችን ለመለየት በ4 አባል ከተሞች በመገኘት ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል። በድርጅቱ የተከናወኑ ስራዎችንና የተለያዩ ትምህርት ሰጪ ተሞክሮዎችን በተለያዩ ሚዲያዎች ተደራሽ በማድረግ የተቋሙን እይታ ከፍ ማድረግ ተችሏል። በመሆኑም የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸምና የተገኙ ውጤቶች የዕቅዱ መነሻ ናቸው።

1.3 ራዕይ፣ተልዕኮና ዕሴቶች

1.3.1 ራዕይ

ዘላቂ ልማት የተረጋገጠባቸው፣ለኑሮ ምቹ፣ አምራች እና ተወዳዳሪ የኢትዮጵያ ከተሞችን ለመፍጠር እሴት የሚጨምር የከተሞች ማህበር መሆን ነው።

1.3.2 ተልዕኮ

- የመልካም አስተዳደር እና ያልተማከለ አስተዳደር መርሆዎችን በማክበር ከተሞች ተልዕኳቸውን እንዲወጡ መደገፍ፤
- ለከተሞች የልምድ ልውውጥ እና የእውቀት ማዕከል በመሆን ማገልገል፤
- ምርጥ ተሞክሮዎችን መለየት፤መቀመርና ለአባል ከተሞች ማሰራጨት፤
- የከተሞችን እህትማማችነት እና ጠንካራ ትብብር ማሳደግ፤

1.3.3 ዕሴቶች

- የላቀ ደረጃ
- *ሙያዊነት*
- ፈጠራ
- ነጻነት
- *የቡድን ስራ*
- *አካታችነት*
- *ተለዋዋጭነት*

1.4 የትብብር መድረኩ የትኩረት አቅጣጫዎች

በ2017 በጀት ዓመት የትብብር መድረኩ የትኩረት አቅጣጫዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

❖ የድርጅቱን ተቋማዊ አቅምና አሰራር ማሳደግ

- የትብብር መድረኩን የአምስት ዓመታት (2015 — 2019 ዓ.ም) ስትራቴጂክ ዕቅድ መሰረት ያደረገ የተቋሙን የመዋቅር ማሻሻያ ጥናት ማካሄድና ከአቅም ጋር በተገናዘበ መልኩ መተግበር፣
- የትብብር መድረኩን የህንጻ መገንቢያ መሬት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መረከብና ለቀጣይ ተግባር ዝግጅት ማድረግ፣
- ለፋይናንስና የሰው ሃይል አቅም ግንባታ መስራት፤
- ዘላቂና አስተማማኝ የፋይናንስ ምንጭ በፋይናንስ ስትራቴጂው መሰረት የኔትወርኪንግና የፕሮጀክት ፕሮፖዛል በማዘጋጀት ከተሞችን ተጠቃሚ የሚያደርግ አሰራር መዘርጋት፤

- የአባል ከተሞችን ቁጥር መጨመር፤

❖ የአባል ከተሞችን የአቅም ግንባታና አገልግሎት አሰጣጥ ማጠናከር

- ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ
- ለከተሞች የእውቀትና አቅም ግንባታ ማዕከል ሆኖ ማገልገል፤

❖ በአገርአቀፍና አለም አቀፍ መድረኮች የአባል ከተሞችን በመወከል የአጋርነትና የኔትወርኪንግ ስራን ማጠናከር

- የባለድርሻ አካላትን በንቃት ማሳተፍ፤
- የድርጅቱን እይታ ከፍ ለማድረግ የኔትወርኪንግና አጋርነትን ማጠናከር፤
- ከከተማና መሰረተ ልማት ሚ/ር፤ ከክልል የከተማና ኮንስትራክሽን ቢሮዎች፤ከአባል ከተሞች እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላትና ከአህጉር አቀፍና አለም አቀፍ መሰል ተቋማት ጋር ጥብቅ ግንኙነትና ትስስር መፍጠር፤
- ከመንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር የትብብር ግንኙነት በመፍጠር ለአባል ከተሞች ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት፤
- አባል ከተሞችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ማድረግ ናቸው።

❖ ለአባል ከተሞች ፍላጎት ዘብ የመቆም ተሳትፎን ማሳደግ

- የከተማ ልማት ፖሊሲ ሃሳቦች አመንጪ ሆኖ መስራት፤
- ለአባል ከተሞች ፍላጎትና ጥቅም ድምጽ መሆን

ክፍል ሁለት፡-

2. የበጀት ዓመቱ ዕቅድ ጥቅል ግብና ዓላማ

2.1 ጥቅል ግብ

ለትብብር መድረኩ አባል ከተሞች አመራርና ባለሙያዎች በከተማ ልማት አጀንዳዎች ዙሪያ የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠትና የልምድ ልውውጥ አውደጥናቶችን በማካሄድ ከተሞች የዕርስ በርስ ግንኙነታቸውን እንዲያጠናክሩ በማድረግ በአህጉር ብሎም በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ይደረጋል።

2.2 ጥቅል ዓላማ

የአባል ከተሞች አመራርና ፈጻሚዎችን የዕውቀትና የክህሎት ክፍተታቸውን በስልጠና፤ በልምድ ልውውጥና በማማከር አገልግሎት በመሙላትና ብቃታቸውን በማሳደግ ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው ምቹ የልማትና የመልካም አስተዳደር ማዕከላት እንዲሆኑ መደገፍና በአገሪቱ ማህበራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ ከፍ ማድረግ ነው፡፡

2.3 ዝርዝር ዓላማዎች

- በተለያዩ የከተማ ነክ ጭብጦች ላይ 3 የልምድ ልውውጥ አውደጥናቶችን በማዘጋጀት በአባል ከተሞች ከንቲባዎችና አመራሮች መካከል የእውቀት፣ የክህሎት እና የልምድ ልውውጥ ማድረግ፡፡

- የትብብር መድረኩ 45 አባል ከተማ ከንቲባዎች እና ተሳታፊዎች በአለም አቀፍ የከተሞች ፎረም እና ልዩ ልዩ ጉባዔዎች ትምህርታዊ ጉዞ በማዘጋጀት እንዲሳተፉ በማድረግ አዳዲስ እውቀቶችን፣ ክህሎቶችን እና ልምዶችን እንዲያገኙ በማድረግ የመፈጸም አቅማቸውን መገንባት፡፡

- ለትብብር መድረኩ አባል ከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች እውቀታቸውን እና ክህሎታውን ለማሳደግ ቁልፍ በሆኑ የከተማ ልማት ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ 6 የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎችን መስጠት።

- የትብብር መድረኩ አባል ከተሞች ያስመዘገቡዋቸውን ስኬቶች፣ ያጋጠሟቸውን ተግዳሮቶች እና ምክረ ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ 2 የፖሊሲ መግለጫዎችን (policy Statement) ማዘጋጀት፤

- የአባልነት መዋጮ ክፍያን አሟጦ መሰብሰብ፤

- የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም የተቋሙ ገጽታና እይታ እንዲጨምር ማድረግ ፣

- በአባል ከተሞች በመገኘት የስልጠናዎች፤አውደጥናቶችና ትምህርታዊ ጉዞዎች ያስገኙትን ውጤትና ያመጡትን ፋይዳ የተመለከተ ክትትልና ግምገማ ማድረግ፤

2.4 በመደበኛ በጀት የሚከናወኑ የፕሮግራም ግቦችና ዝርዝር ተግባራት

2.4.1 የልምድ ልውውጥና እውቀት ሽግግርን በተመለከተ

2.4.1.1 የአገር ውስጥ አውደጥናትና ልምድ ልውውጥ

ግብ 1፡- "በማዘጋጃቤታዊ ገቢ እና በአገልግሎት አሰጣጥ" ዙሪያ ያተኮረ በ100 አባል ከተሞች መካከል አንድ የልምድ ልውውጥ አውደ ጥናት ይካሄዳል፡፡

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ዝግጅት፤

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- ለአውደ ጥናቱ የሚሆኑ መልካም ተሞክሮዎችን መለየት፤

ተግባር 4፡- ከተሞች መልካም ተሞክሮዎቹን ቀምረው እንዲልኩ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፤

ተግባር 5፡- ተሞክሮዎቹን ከከተሞች መሰብሰብ፤

ተግባር 6፡- ከከተሞች የተሰበሰቡ ተሞክሮዎችን ማረም፤ ለህትመት ዝግጁ ማድረግ፤

ተግባር 7፡- ለአውደ ጥናቱ የስብሰባ ቦታና ለተግባር ምልከታ የሚያመች ከተማ መለየት፤

ተግባር 8፡- በአውደጥናቱ የሚገኙ ተሳታፊዎችን ጥሪ ማድረግና አውደ ጥናቱን ማካሄድ፤

ተግባር9 ፡- ሪፖርት ማዘጋጀት

ግብ 2፡- የከተሞች ወርን (Urban October Event) ምክንያት በማድረግ "በወቅታዊ የከተማ ልማት አጀንዳ" ዙሪያ ያተኮረ በ100 አባል ከተሞች መካከል አንድ የልምድ ልውውጥ አውደጥናት ይካሄዳል፡፡

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ዝግጅት፤

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- ለአውደ ጥናቱ የሚሆኑ መልካም ተሞክሮዎችን መለየት፤

ተግባር 4፡- ተሞክሮዎቹን መቀመር፤

ተግባር 5፡- ተሞክሮዎቹን ማሳተም፤

ተግባር 6፡- ለአውደ ጥናቱ የስብሰባ ቦታና ለተግባር ምልከታ የሚያመች ከተማ መለየት፤

ተግባር 7፡- በአውደጥናቱ የሚገኙ ተሳታፊዎችን ጥሪ ማድረግና አውደ ጥናቱን ማካሄድ፤

ተግባር 8 ፡- ሪፖርት ማዘጋጀት

ግብ 3፡- "በተመረጡ የከተማ ከንቲባ ስኬቶች፣ ተግዳሮቶች እና እድሎች" ዙሪያ ያተኮረ በ100 አባል ከተሞች መካከል አንድ የልምድ ልውውጥ አውደ ጥናት ይካሄዳል፡፡

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ዝግጅት፤

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- ለአውደ ጥናቱ የሚሆኑ መልካም ተሞክሮዎችን መለየት፤

ተግባር 4፡- ከተሞች መልካም ተሞክሮዎቹን ቀምረው እንዲልኩ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፤

ተግባር 5፡- ተሞክሮዎቹን ከከተሞች መሰብሰብ፤

ተግባር 6፡- ከከተሞች የተሰበሰቡ ተሞክሮዎችን ማረም፤ ለህትመት ዝግጁ ማድረግ፤

ተግባር 7፡- ለአውደ ጥናቱ የስብሰባ ቦታና ለተግባር ምልከታ የሚያመች ከተማ መለየት፤

ተግባር 8፡- በአውደጥናቱ የሚገኙ ተሳታፊዎችን ጥሪ ማድረግና አውደ ጥናቱን ማካሄድ፤

ተግባር 9 ፡- ሪፖርት ማዘጋጀት

ግብ 4፡- ነባር የትብብር መድረኩ አባል ከተማ ከንቲባዎችን አዲስ ከሚሾሙ የትብብር መድረኩ አባል ከተማ ከንቲባዎች ጋር ለሙያዊ ምክርና ድጋፍ አሰጣጥ (Coaching & Mentoring) የአንድ ለአንድ ጥምርታ እንዲፈጠር በማድረግ አዳዲስ ከንቲባዎች ልምድ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

ተግባር 1፡- የሙያዊ ምክርና ድጋፍ አሰጣጥ ማንዋል ይዘጋጃል፤

ተግባር 2፡- በሰነዱ ላይ ለአባል ከተማ ከንቲባዎች ገለጻ ይደረጋል፤

ተግባር 3፡- ልምድ ያላቸውን ድጋፍ ሊሰጡ የሚችሉ የትብብር መድረኩ አባል ከተማ ነባር ከንቲባዎች ይለያሉ፤

ተግባር 4፡- ድጋፍ የሚሹ የትብብር መድረኩ አባል ከተማ አዳዲስ ከንቲባዎች ይለያሉ፤

ተግባር 5፡- ድጋፍ ሰጪ (mentor) እና ድጋፍ ተቀባይ (mentee) የትብብር መድረኩ አባል ከተማ ከንቲባዎች ትስስር እንዲፈጥሩ ይደረጋል፤

ተግባር 6፡- የእርስ በርስ ተሞክሮ ልውውጥ እንዲያደርጉ ማበረታታት፤

ግብ 5፡- የይርጋለም ከተማ የማዘጋጃቤታዊ ገቢ ተሞክሮን በ4 በተመረጡ ከተሞች የማስፋትና የማስተግበር ፕሮጀክት ስራ ይከናወናል፡፡

ተግባር 1፡- ተሞክሮው ሊሰፋባቸው የሚችሉ ከተሞችን መለየት፤

ተግባር 2፡- ለተመረጡ ከተሞች ተገቢውን የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፤

ተግባር 3፡- የትግበራ ሂደቱን ክትትል ማድረግ፤

ተግባር 4፡- በተደረገው ክትትል መሰረት ተገቢውን ግብረ መልስ መስጠት

2.4.1.2 የውጭ አገር ልምድ ልውውጥ

ግብ 6፡- ከኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ አባል ከተማ ከንቲባዎች የተውጣጡ 15 ተሳታፊዎች ከጥቅምት 25-29/2017 ዓ.ም በግብፅ ካይሮ ከተማ በሚካሄደው 12ኛው የአለም የከተሞች ፎረም (”World Urban Forum”) ላይ በመሳተፍ የተሞክሮ የልምድ ልውውጥ እንዲያካሂዱ ይደረጋል፡፡

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ዝግጅት፤

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- ለተመረጡ ተሳታፊዎች የግብዣ ደብዳቤ ("invitation letter") እንዲመጣላቸው ማድረግ፤

ተግባር 4፡- ለተሳታፊዎች ቪዛ እንዲያገኙ ማመቻቸት፤

ተግባር 5፡- ለተሳታፊዎች ጥሪ ማስተላለፍ፤

ተግባር 6፡- 15 ከንቲባዎችና ተሳታፊዎች በአለም የከተሞች ፎረም ግብጽ ካይሮ ተገኝተው እንዲሳተፉ ማድረግ፤

ተግባር 7፡- በከተሞቻችን ሊተገበሩ የሚችሉ የተሞክሮ ዘርፎችን (thematic issues) መለየት፤

ተግባር 8፡- መረጃዎችን ማደራጀት፣ ማጠናከር፣ መተንተንና ረቂቅ የተሞክሮ ሰነድ ማዘጋጀት፤

ተግባር 9፡- በተዘጋጀው የተሞክሮ ሰነድ ግብዓት ማሰባሰብ፤

ተግባር 10፡- ሰነዱን በማዳበር የመጨረሻ ቅርጽ ማስያዝ፤

ተግባር 11፡- የተሞክሮ ሰነዱን ለትግበራ ለአባል ከተሞች ተደራሽ ማድረግ፤

ግብ 7፡- ከኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ አባል ከተማ ከንቲባዎች የተውጣጡ 10 ተሳታፊዎች ”በስማርት ሲቲ ጽንሰ ሃሳብና ትግበራ (Smart City Concept and Implementation)” ዙሪያ በተመረጠ አገር ትምህርታዊ የልምድ ልውውጥ (Study Visit) እንዲያካሂዱ ይደረጋል፡፡

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ዝግጅት፤

ተግባር 2፡- በዝክረ ተግባሩ መሰረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- ለተመረጡ ተሳታፊዎች የግብዣ ደብዳቤ ("invitation letter") እንዲመጣላቸው ማድረግ፤

ተግባር 4፡- ለተሳታፊዎች ቪዛ እንዲያገኙ ማመቻቸት፤

ተግባር 5፡- የልምድ ልውውጥ የድርጊት መርሃግብር ይዘጋጃል፤

ተግባር 6፡- ለተሳታፊዎች ጥሪ ማስተላለፍ፤

ተግባር 7፡- 10 ተሳታፊዎች በተመረጠው አገር በአካል በመሄድ የልምድ ልውውጥ /Experience Exchange Study Visit/ ያደርጋሉ፤

ተግባር 8፡- በከተሞቻችን ሊተገበሩ የሚችሉ የተሞክሮ ዘርፎችን (thematic issues) መለየት፤

ተግባር 9፡- መረጃዎችን ማደራጀት፣ ማጠናከር፣ መተንተንና ረቂቅ የተሞክሮ ሰነድ ማዘጋጀት፤

ተግባር 10፡- በተዘጋጀው የተሞክሮ ሰነድ ግብዓት ማሰባሰብ፤

ተግባር 11፡- ሰነዱን በማዳበር የመጨረሻ ቅርጽ ማስያዝ፤

ተግባር 12፡- የተሞክሮ ሰነዱን ለትግበራ ለአባል ከተሞች ተደራሽ ማድረግ፤

ግብ 8፡- ከኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ አባል ከተማ ከንቲባዎች የተውጣጡ 20 ተሳታፊዎች በተለያዩ አለም አቀፍ ጉባኤዎች እና የልምድ ልውውጥ መድረኮች ላይ እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ዝግጅት፤

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- ለተመረጡ ተሳታፊዎች የግብዣ ደብዳቤ ("invitation letter") እንዲመጣላቸው ማድረግ፤

ተግባር 4፡- ለተሳታፊዎች ቪዛ እንዲያገኙ ማመቻቸት፤

ተግባር 5፡- ለተሳታፊዎች ጥሪ ማስተላለፍ፤

ተግባር 6፡- 20 ከንቲባዎችና ተሳታፊዎች በጉባኤዎች እና ልዩ ልዩ መድረኮች እንዲሳተፉ ማድረግ፤

ተግባር 7፡- በከተሞቻችን ሊተገበሩ የሚችሉ የተሞክሮ ዘርፎችን (thematic issues) መለየት፤

ተግባር 8፡- መረጃዎችን ማደራጀት፣ ማጠናከር፣ መተንተንና ረቂቅ የተሞክሮ ሰነድ ማዘጋጀት፤

ተግባር 9፡- በተዘጋጀው የተሞክሮ ሰነድ ግብዓት ማሰባሰብ፤

ተግባር 10፡- ሰነዱን በማዳበር የመጨረሻ ቅርጽ ማስያዝ፤

ተግባር 11፡- የተሞክሮ ሰነዱን ለትግበራ ለአባል ከተሞች ተደራሽ ማድረግ፤

2.4.2 የአቅም ግንባታ ስልጠናን በተመለከተ፤

ግብ 9፡- ለ30 የአማራ ክልል ከተሞች ከንቲባዎችና የክልል የስራ ሃላፊዎች "በUrban Resilience" እና "በቅርስ ጥበቃ እና ቱሪዝም ልማት" (Historical site preservation and tourism development) **ላይ ስልጠና ይሰጣል፡፡**

ተግባር 1፡- የስልጠና ዝክረ ተግባር ማዘጋጀት፤

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- የስልጠና ሰነድ ዝግጅት እና ግምገማ፤

ተግባር 3፡- የስልጠና ቦታና ከተማ መምረጥ፤

ተግባር 4፡- ለስልጠና ተሳታፎች ጥሪ ማስተላለፍ፤

ተግባር 5፡- ለ30 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ይሰጣል፤

ተግባር 6 ፡- ሪፖርት ማዘጋጀት

ግብ 10፡- ለ30 የኦሮሚያ ክልል ከተሞች ከንቲባዎችና የክልል የስራ ሃላፊዎች "በመልካም አስተዳደርና ሰላም ግንባታ (good governance and peacebuilding) **እንዲሁም በአካታች የከተማ ፕላኒንግ** (Inclusive Urban Planning)" **ላይ ስልጠና ይሰጣል፡፡**

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ዝግጅት፤

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- የስልጠና ቦታና ከተማ መምረጥ፤

ተግባር 4፡- ሰልጣኞችን መለየትና ጥሪ ማስተላለፍ፤

ተግባር 5፡- ለ30 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ይሰጣል፤

ተግባር6 ፡- የአፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት

ግብ 11፡- ለ30 የሶማሌ ክልል ከተሞች ከንቲባዎችና የክልል የስራ ሃላፊዎች በ"Urban Resilience"፤ በማዘጋጃቤታዊ ገቢ ስርዓት፤ በአገልግሎት አሰጣጥ እና በህዝብ ተሳትፎ ዙሪያ ስልጠና ይሰጣል፡፡

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ዝግጅት፤

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- የስልጠና ቦታና ከተማ መምረጥ፤

ተግባር 4፡- ሰልጣኞችን መለየትና ጥሪ ማስተላለፍ፤

ተግባር 5፡- ለ30 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ይሰጣል፣

ተግባር 6 ፡- የአፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት

ግብ 12፡- ለ30 የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልልና የሲዳማ ክልል ከተሞች ከንቲባዎችና የክልል የስራ ሃላፊዎች "በመልካም አስተዳደርና ሰላም ግንባታ (good governance and peacebuilding)፣ **በአካታች የከተማ ፕላኒንግ** (Inclusive Urban Planning)" **ላይ ስልጠና ይሰጣል፡፡**

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ዝግጅት፣

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፣

ተግባር 3፡- የስልጠና ቦታና ከተማ መምረጥ፣

ተግባር 4፡- ሰልጣኞችን መለየትና ጥሪ ማስተላለፍ፣

ተግባር 5፡- ለ30 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ይሰጣል፣

ተግባር6 ፡- የአፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት

ግብ 13፡- ለ30 የደቡብ ምዕራብ፤ የአፋር፤ የቤኒሻንጉል፤ የድሬዳዋ፤ ሐረር እና ጋምቤላ ክልል ከተሞች ከንቲባዎችና የክልል የስራ ሃላፊዎች "በመልካም አስተዳደርና ሰላም ግንባታ (good governance and peacebuilding) **እንዲሁም በአካታች የከተማ ፕላኒንግ** (Inclusive Urban Planning)" **ላይ ስልጠና ይሰጣል፡፡**

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ዝግጅት፣

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፣

ተግባር 3፡- የስልጠና ቦታና ከተማ መምረጥ፣

ተግባር 4፡- ሰልጣኞችን መለየትና ጥሪ ማስተላለፍ፣

ተግባር 5፡- ለ30 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ይሰጣል፣

ተግባር6 ፡- የአፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት

ግብ 14፡- ለ30 የትግራይ ክልል ከተሞች ከንቲባዎችና የክልል የስራ ሃላፊዎች "የከተማ ከንቲባ እና የህዝብ አስተዳደር፣ የማዘጋጃቤታዊ ገቢና ፋይናንስ ስርዓት፣ የቅርስ ጥበቃ እና የከተማ ግብርና" ዙሪያ ስልጠና ይሰጣል፡፡

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ዝግጅት፣

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፣

ተግባር 3፡- የስልጠና ቦታና ከተማ መምረጥ፣

ተግባር 4፡- ሰልጣኞችን መለየትና ጥሪ ማስተላለፍ፣

ተግባር 5፡- ለ20 አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ይሰጣል፣

ተግባር6 ፡- የአፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት

2.4.3 የሃብት ማፈላለግና ኔትወርኪንግ ሰራዎችን በተመለከተ

ግብ 15፡- በለጋሽ ድርጅቶች በሚወጡ ማስታወቂያዎች መሰረት አምስት የሃብት ማፈላለጊያ ኮንሴፕት ኖቶች እና ፕሮፖዛሎች ይዘጋጃሉ፤ አምስት ሚሊዮን ብር የሃብት ድጋፍ ይገኛል።

ተግባር 1፡- ማስታወቂያ መከታተል፣

ተግባር 2፡- ማስታወቂያ ያወጣውን ዶነር አስፈላጊ ሰነዶች ማንበብና መረዳት፣

ተግባር 3፡- በፎርማቶቹ መሰረት ኮንሴፕት ኖት ማዘጋጀት፣

ተግባር 4፡- ለአስተያየት ዝግጁ ማድረግ፣ አስተያየቶችን ማሰባሰብ፣

ተግባር 5፡- በተሰጡ አስተያየቶች መሰረት ሰነዱን ማዳበር፣

ተግባር 6፡- ለውድድር ማመልከት፣

ተግባር 7፡- የውድድር ሂደቱንና ውጤቱን መከታተል፣

ተግባር 8፡ ውል መፈራረምና ትግበራ መጀመር፤

ተግባር 9፡ የፕሮጀክት አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት

ግብ 16፡- ከተለያዩ የአገር ውስጥና የውጭ አገር መሰል ተቋማትና ድርጅቶች ጋር የስራ ግንኙነትና የአጋር አካላት ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡

ተግባር 1፡- የቁልፍ ባለድርሻ አካላት ልየታ ማድረግ፤

ተግባር 2፡- ከተለያዩ አገር አቀፍና አለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር አብሮ መስራት በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ የመግባቢያ ስምምነት መፈራረም፣

ተግባር 3፡- በስምምነቱ መሰረት መደበኛ የግንኙነት ጊዜ በማስቀመጥ አፈጻጸሙን መገምገም፤

ግብ 17፡-የአባል ከተሞችን የእህትማማችነት ቁርኝት ከፍ ለማድረግና ከመሰል የውጪ ከተሞች ጋር ያላቸውን ትስስር ለማሳደግ 5 ከተሞችን በአገር ውስጥና 2 ከተሞችን ደግሞ ከውጪ አገር ከተሞች ጋር የማስተሳሰር ስራ ይከናወናል፡፡

ተግባር 1፡- እህት ከተማ ያላቸውን የአገራችን ከተሞች ያሉበትን ደረጃ የሚያሳይ መረጃ መሰብሰብና ማጠናከር

ተግባር 2፡- ለእህት ከተማ የሌላቸውን አባል ከተሞች ፍላጎታቸውን በማጥናት ከውስጥና ከውጭ ከተሞች ጋር ትስስር መፍጠር፤

ተግባር 3፡- በእህት ከተሞች ግንኙነት ዙሪያ የተገኘውን ውጤት ክትትልና ግምገማ ማድረግ፤

ተግባር 4፡- የእህትማማችነት ትስስር ማድረጊያ የአሰራር ማኑዋል በማዘጋጀት ለከተሞች ተደራሽ ማድረግ፤

2.4.4 የኮሙኒኬሽን ስራዎች በተመለከተ

ግብ 18፡-የትብብር መድረኩን መልካም ገጽታና እይታ ጠብቆ ለማቆየትና ከፍ ለማድረግ 2 የቴሌቪዥን ፓናል ውይይት ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት የትብብር መድረኩ አገልግሎቶች ይተዋወቃሉ፡፡

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ማዘጋጀትና ማጸደቅ

ተግባር 2፡- ከትብብር መድረኩ ጋር መስራት የሚፈልጉ የሚዲያ ተቋማትን መለየት፣

ተግባር 3፡- የትብብር መድረኩን ተግባራትንና የአባል ከተሞችን ግንዛቤ ሊያሰፋ የሚችል የፓናል ውይይት አጀንዳዎችን መቅረጽ፣

ተግባር 4፡- ለባለድርሻ አካላትና በአጠቃላይ ለህብረተሰቡ ዘንድ ተደራሽ ሊያደርጉ የሚችሉ ልምድ ያላቸው የፓናል ውይይት አቅራቢዎችን መለየት፤

ተግባር 5፡- የተላለፉ ፕሮግራሞችን ምስልና ድምጽ ዶክመንት ማድረግ

ግብ 19፡- የትብብር መድረኩን አገልግሎቶች የሚያስተዋውቅና ተቋሙ በከተማ ልማት ዘርፍ ለአባል ከተሞች የሰጣቸውን አውደጥናቶችና ስልጠናዎች መሬት መውረዳቸውንና ስኬታማነታቸውን የሚዳስስ የ15 ደቂቃ ዶክመንተሪ ፊልም ይዘጋጃል፡፡

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ማዘጋጀትና ማጸደቅ

ተግባር 2፡- የተሳካ አተገባበር ያላቸውን ከተሞች መምረጥና መለየት

ተግባር 3፡- በዶክመንተሪ ፊልም አዘገጃጀት ከፍተኛ ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች መቅጠር፣

ተግባር 4፡- ለስክሪፕት የሚረዱ አስፈላጊ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣

ተግባር 5፡- የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን ማከናወን፣

ተግባር 6፡- የተዘጋጀውን ዶክመንተሪ መገምገም፣

ተግባር 7፡- ዶክምንተሪ ፊልሙን ለተገቢው ዓላማ ማዋል፣

ግብ 20፡-የትብብር መድረኩ በሚያዘጋጀቸው 6 ስልጠናዎችና 3 የአገር ውስጥ የልምድ ልውውጥ አውደጥናቶች ላይ ጋዜጠኞችን በመጋበዝ የዘገባ፣ የቀረጻና የዶክመንቴሽን እንዲሁም የህትመትና ስርጭት ስራዎች በማከናወን የተቋሙ ገጽታና እይታ እንዲጨምር ይደረጋል ፣

ተግባር 1፡- የተለያዩ ሚዲያዎች እንዲገኙ ጥሪ ማድረግ፤፣

ተግባር 2፡- ለተጋበዙ ሚዲያዎች የአዘጋገብ ሁኔታዎችን በሚመለከት አጭር ገለጻ ማድረግ

ተግባር 3፡- ቃለ መጠየቅ የሚሰጡ ሰዎችን በመምረጥ የትብብር መድረኩን መልካም ገጽታ በሚገነባ መልኩ ቃለ ምልልስ እንዲያደርጉ ምክረ ሃሳብ ማቅረብ፣

ተግባር 4፡- ትብብር መድረኩን በሚመለከት የወጡ ዘጋባዎችን ማሰባሰብና የዶክመንቴሽን ስራ ማከናወን፤

ተግባር 5፡- ተቋሙን በተመለከተ በተለያዩ የሚዲያ ተቋማት የሚወጡ መረጃዎችን በየጊዜው ክትትል በማድረግ የሚዲያ ሞኒተሪንግ ስራ ማከናወን፤

ተግባር 6፡- የትብብር መድረኩን ገጽታና እይታ የሚጨምሩ መልዕክቶችን በተቋሙ የተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች እንዲተላለፉና ዌብሳይት ላይ እንዲጫኑ ማድረግ፣

ተግባር 7፡- ትብብር መድረኩን በተመለከተ በተለያዩ ሚዲያዎች የተላለፉ ኦዲዮ ቪዥዋል ማቴሪያሎችን ዶክመንት ማድረግ፣

ተግባር 8፡-የትብብር መድረኩን አገልግሎቶች ለማስተዋወቅ ህትመትና ስርጭት ማካሄድ፤

ተግባር 9፡- የስልጠናዎች፣ አውደ ጥናቶች፣ የፓናል ውይይቶችና የምክክር መድረኮች የዘገባ ዜና በማህበራዊ ሚዲያ ማቅረብ፣

ተግባር 10፡- የትብብር መድረኩ የሚሰጡ የስልጠናና የአውደጥናት ሰነዶች እና ሌሎች ለእውቀት ሽግግር የሚያግዙ ሰነዶች በትብብር መድረኩ በይነ መረብ ላይ መጫንና ተደራሽ ማድረግ፤

ግብ 21፡- የትብብር መድረኩን አገልግሎቶችና አጠቃላይ ገጽታ የሚያስተዋውቅ ሳምንታዊና ወርሃዊ ዲጂታል ዜና መጽሄት ይዘጋጃል፡፡

ተግባር 1፡ ዝክረ ተግባር ማዘጋጀትና ማጸደቅ፤

ተግባር 2፤ ኤዲቶሪያል ኮሚቴ ማቋቋም፡

ተግባር 3፡ አመታዊ መጽሄት አዘጋጅ አማካሪ መቅጠር፤

ተግባር 4፤ የህትመት ይዘትና ዲዛይን ላይ ግምገማ ማካሄድና ማጽደቅ፡

ተግባር 5. የህትመት ስራዎችን መከታተል፡

ተግባር 6. የህትመት ውጤቶችን መረከብና ማሰራጨት፡፡

ግብ 22፡- የትብብር መድረኩ የአባል ከተሞች ቁጥር አሁን ካለበት 96 ወደ126 ለማሳደግ ሶስት የምክክር መድረኮች በማዘጋጀት 30 አዳዲስ አባል ከተሞች ሙሉ አባል ይደረጋሉ፡፡

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ማዘጋጀትና ማጸደቅ፣

ተግባር 2፡ ተሳታፊዎችንና ቦታ መለየት፣

ተግባር 3፡ ሎጀስቲክስና ሆቴል ማመቻቸት፣

ተግባር 4፡ ጥሪ ማስተላለፍ፣

ተግባር 5፡ አባል መሆን የሚችሉ ከተሞችን በየክልሉ በመለየት እና በማደራጀት መድረክ ማዘጋጀትና የትብብር መድረኩ ዓላማ፤ ተልዕኮ እና የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ማስተዋወቅና ወደ አባልነት እንዲመጡ መቀስቀስ፣

ተግባር 6፡- የአባልነት መስፈርቱን ማሟላት የቻሉትን ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በማቅረብ ማጸደቅ፣

ተግባር 7፡- አባል ለሚሆኑ እና ክፍያቸውን ለሚያጠናቅቁ አባል ከተሞች የምስጋና ደብዳቤና ደረሰኝ በወቅቱ መላክ፣

ተግባር 8፡- የትብብር መድረኩ አባል መሆናቸውን የሚገልጽ የእንኳን ደስ አላችሁ የሚል መልዕክት በመቅረጽ እንዲተላለፍ ማድረግ፣

ተግባር 9፡- ሪፖርት ማቅረብ፣

ግብ 23፡- በአባል ከተሞች ለሚገኙ 125 የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት ኃላፊዎች በማናጀሪያል ኮሙዩኒኬሽን ዙሪያ ስልጠና ይሰጣል።

ተግባር 1፡- የስልጠናውን ዝክረ ተግባር ማዘጋጀት፣

ተግባር 2፡- በስልጠናው ላይ ተሳታፊ የሚሆኑ አካላትን መለየት፣

ተግባር 3፡- የስልጠናውን ቦታ መለየት፣

ተግባር 4፡- ተሳታፊዎችን ጥሪ ማድረግና ስልጠናውን ማካሄድ፣

ተግባር 5፡- የስልጠናውን አካሄድና ያስገኘውን ለውጥ መገምገምና ሪፖርት ማዘጋጀት ።

ግብ 24፡- የትብብር መድረኩ አባል ከተሞች ያስመዘገቡዋቸውን ስኬቶች፣ ያጋጠሟቸውን ተግዳሮቶች እና ምክረ ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ 2 የፖሊሲ መግለጫዎች (policy statement) ይዘጋጃሉ፤

ተግባር 1፡- አባል ከተሞችን እና ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ቁልፍ የከተማ ነክ ጉዳዮችን ለፖሊሲ መግለጫዎች (Policy statement) እና ምክረ-ሃሳብ መለየት፤

ተግባር 2፡- በየሩብ ዓመቱ የፖሊሲ መግለጫ እና ምክረ-ሃሳብ የሚሰጥባቸውን የተወሰኑ የከተማ ነክ ርእሶችን በመመደብ የዓመቱን መርሃ ግብር ማዘጋጀት፤

ተግባር 3፡- ለእያንዳንዱ ርእሰ ጉዳይ ነባራዊ ሁኔታውን በጥልቀት ለመረዳት በናሙናነት የተመረጡ የከተማ ከንቲባዎችን፣ የዘርፉ ባለሙያዎችን እና ተመራማሪዎችን ኢንተርቪው ማድረግ፤

ተግባር 4፡- በተመረጠው ርእሰ ጉዳይ የስነ-ጽሁፍ ግምገማዎችን (literature review) ማካሄድ እና የጥናት ግኝቶችን ማሰባሰብ፤

ተግባር 5፡- በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ እና ተግባር ላይ ያተኮሩ አጫጭር ረቂቅ የፖሊሲ መግለጫዎች እና ምክረ-ሃሳቦች ይዘጋጃሉ፤

ተግባር 6፡- ወጥነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ደረጃውን የጠበቀ የፖሊሲ መግለጫ እና ምክረሀሳብ የሚሰጥበትን ፎርማት ማዘጋጀት፤

ተግባር 7፡- የተዘጋጁት ረቂቅ የፖሊሲ መግለጫዎች እና ምክረ-ሃሳቦች ለስራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላት ለአስተያየት ይሰራጫል፤

ተግብር 8፡- በየሩብ ዓመቱ በሚዘጋጁ ስልጠናዎች እና የልምድ ልውውጥ መድረኮች ላይ የፖሊሲ መግለጫው እና ምክረ-ሃሳብ ለተሳታፎች ይቀርባል፤ ውይይት ይደረግበታል፤

ተግባር 9፡- ረቂቅ የፖሊሲ መግለጫውን እና ምክረ-ሃሳብ የመጨረሻ ቅርፅ በማስያዝ በትብብር መድረኩ ዌብሳይት እና ማህበራዊ ሚዲያዎች ይሰራጫል፤

ተግባር 10፡- በየሩብ ዓመቱ የተዘጋጁ የፖሊሲ መግለጫዎች እና ምክረ-ሃሳቦች ይጠመራሉ፤

ግብ 25፡- በአውደጥናቶች የሚቀርቡ ተሞክሮዎችን በማሳተም ለአባል ከተሞች እንዲሰራጭ ይደረጋል፡፡

ተግባር 1፡- በምርጥ ተሞክሮ መለያ መስፈርት መሰረት ተሞክሮዎች እንዲለዩና እንዲቀመሩ ማድረግ፣

ተግባር 2፡- ተቀምሮ የመጣውን ሰነድ ኤዲት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- የተቀመረውን ተሞክሮ ሰነድ በማሳተም ለአባል ከተሞች ማሰራጨት፤

2.4.5 የፕሮግራምና የፕሮጀክት ስራዎች የክትትልና ግምገማ ተግባራት

ግብ 26፡- የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ ውጤትን መሰረት ያደረገ የክትትልና ግምገማ ማኑዋል ይዘጋጃል፡፡

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ዝግጅት፣

ተግባር 2፡- አማካሪ ቅጥር መፈጸም

ተግባር 3፡- የሰነድ ዝግጅቱን ክትትል ማድረግ፣

ተግባር 4፡- የግብዓት ማሰባሰቢያና ማጸደቂያ አውደጥናት ማዘጋጀት፣

ግብ 27፡-በተመረጡ 9 አባል ከተሞችና ከተማ ልማት ቢሮዎች በመገኘት የስልጠናዎች፤ አውደጥናቶችና ትምህርታዎ ጉዞዎች ተግባራዊነትና ያመጡትን ፋይዳ የተመለከተ ክትትልና ግምገማ ይደረጋል፡፡

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ማዘጋጀት፣

ተግባር 2፡- የክትትል፤ ድጋፍና ግምገማ ቼክ ሊስት ማዘጋጀት፣

ተግባር 3፡- በተዘጋጀው ቼክ ሊስት መሰረት በከተሞችና ቢሮዎች በመገኘት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣

ተግባር 4፡- ከተሞች በቀሰሙት እውቀትና ልምድ መሰረት እቅድ አዘጋጅተው እየተንቀሳቀሱ መሆኑን መመልከት፤

ተግባር 5፡- የተገኙ መልካም ልምዶችን መለየትና የተለየውን መልካም ተሞክሮ ለመቀመር የሚያስችል መረጃ ማሰባሰብ፣

ተግባር 6፡- የተሰበሰበውን መረጃ መሰረት በማድረግ የጽሑፍ ግብረ መልስ በማዘጋጀት ለከተሞች ማሰራጨት፣

ተግባር 7፡- የክትትልና ግምገማ ሪፖርት ማዘጋጀት

2.5 በፕሮጀክት በጀት የሚከናወኑ የፕሮግራም ግቦችና ዝርዝር ተግባራት

ፕሮጀክት አንድ፡- የአባል ከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች የስልጠና እና የልምድ ልውውጥ ስራ ፕሮጀክት /ULGE: Uniting Local Governments in Ethiopia Project/፤

ግብ1፡- በናሙናነት በተመረጡ ከተሞች የዘርፉን ቁልፍ የአፈጻጸም አመላካቾችን (key performance indicators) **መሰረት በማድረግ የመነሻ ሁኔታ መረጃዎችን** (baseline data) **በማሰባሰብ 1 ጥናታዊ ሰነድ** (Ethiopian Cities Dashboard) **ይዘጋጃል፡፡**

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ዝግጅት፤

ተግባር 2፡- በዝክረ-ተግባሩ መሠረት የሎጂስቲክስ ዝግጅት ማድረግ፤

ተግባር 3፡- የ"Ethiopian Cities Dashboard" አዘጋጅ አማካሪ ተቋማት ጋር ውይይት ማድረግ፤

ተግባር 4፡- ከአማካሪ ተቋማት ጋር የስራ ውል መፈጸም፤

ተግባር 5፡- በውሉ መሰረት ስራው ስለመፈጸሙ የሱፐርቪዥን ስራዎችን ማከናወን፤

ተግባር 6፡- የ"Ethiopian Cities Dashboard" ዝግጅት ማጠናቀቅ፤

ግብ 2፡- በአባል ከተሞችና ከተማ ልማት ቢሮዎች በመገኘት ምርጥ ተሞክሮዎችን መለየት፤ ተሞክሮ መቀመር እና አዳዲስ አባላትን ለመጨመር የማግባባት ስራ ይሰራል፡፡

ተግባር 1፡- ዝክረ ተግባር ማዘጋጀት፤

ተግባር 2፡- ተሞክሮ ልየታ ማድረግ፤

ተግባር 3፡- የተሞክሮ መቀመሪያ ቼክሊስት ማዘጋጀት፤

ተግባር 4፡- ከክልል የከተማ ልማት ዘርፍ ቢሮ ሃላፊዎች እና ከንቲባዎች ጋር መወያየት፤

ተግባር 5፡- ተሞክሮ ለመቀመር የሚያስችል መረጃ ማሰባሰብ፣

ተግባር 6፡- የተሰበሰቡ መረጃዎችን ማደራጀት፣ ማጠናከር፣ መተንተንና ረቂቅ የተሞክሮ ሰነድ ማዘጋጀት፤

ተግባር 7፡- በተዘጋጀው ረቂቅ የተሞክሮ ሰነድ ግብዓት ማሰባሰብ፤

ተግባር 8፡- ሰነዱን በማዳበር የመጨረሻ ቅርጽ ማስያዝ፤

ተግባር 9፡- የተሞክሮ ሰነዱን ለትግበራ ለአባል ከተሞች ተደራሽ ማድረግ፤

ግብ 3፡- የትብብር መድረኩ ተቋማዊ የመዋቅር ማሻሻያ ጥናት ይካሄዳል፡፡

ተግባር 1፡- ዝክረተግባር ዝግጅት፤

ተግባር 2፡- አማካሪ ቅጥር መፈጸም፤

ተግባር 3፡- የሰነድ ዝግጅቱን ክትትል ማድረግ፤

ተግባር 4፡- የግብዓት ማሰባሰቢያና ማጸደቂያ አውደጥናት ማዘጋጀት፤

ግብ 4፡- የ ULGE ፕሮጀክት 100 ቡክሌት ህትመት ይከናወናል፡፡

ተግባር 1፡- ለቡክሌት ዝግጅት ጽሁፍ ማርቀቅ፤

ተግባር 2፡- በተዘጋጀው ጽሁፍ ግብዓት ማሰባሰብ፤

ተግባር 3፡- ጽሁፉን በማዳበር የመጨረሻ ቅርጽ ማስያዝ፤

ተግባር 4፡- ቡክሌት ማሳተም እና ለአባል ከተሞች ተደራሽ ማድረግ፤

2.6 የአስተዳደርና ፋይናንስ ሰራዎች

ግብ 1፡-ከነባርና አዲስ አባል ከተሞች ብር 40,350,000.00 ገቢ ይሰበሰባል፡፡

ተግባር 1፡- ከነባር አባል ከተሞች የተመደበላቸውን አመታዊ መዋጮ እና ውዝፍ በጀት እንዲይዙ የሚገልጽ ደብዳቤ በመጻፍ ብር 37,200,000.00 ይሰበሰባል፤

ተግባር 2፡-በደብዳቤ፣ በስልክና በአካል በመንቀሳቀስ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት ከአባል ከተሞች የገቢ ማሰባሰቢያ ስራ መስራት፣

ተግባር 3፡- ትብብር መድረኩን ከሚቀላቀሉ 30 አዲስ ከተሞች ብር 3,150,000.00 ይሰበሰባል፤

ተግባር 4፡-ክፍያቸውን ለፈጸሙ ነባርና አዲስ ከተሞች የምስጋና ደብዳቤና ደረሰኝ መላክ፤

ግብ 2. ከአገር ውስጥ የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሃብት ድጋፍ ለማግኘት የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በአጋርነት አብረው እንዲሰሩ በማድረግ 3,000,000.00 ብር ይሰበሰባል፤

ተግባር 1. የሃብት ማፈላለጊያ ስፖንሰርሺፕ ፕሮፖዛል ማዘጋጀት

ተግባር 2. የጋራ ስምምነት (Memorandum of Understanding) መፈራረም፤

ተግባር 3. በወጪ መጋራት መርህ ከከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ማድረግና የጋራ ዝክረ ተግባር ማዘጋጀት፤

ግብ 3. ከውጭ አገር ነባር (ULGE) የፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሃብት ድጋፍ 1,617,138.56 ብር ይሰበሰባል፤

ተግባር 1፡- በፕሮጀክት ስምምነት መሰረት ተገቢውን ዓመታዊ ዝርዝር እቅድ ማዘጋጀት

ተግባር 2፡- በቀረበውና በጸደቀው ዕቅድ መሰረት የበጀት መጠየቂያ ማዘጋጀትና ማቅረብ፣

ተግባር 3፡- የአፈጻጸም ሪፖርት ጊዜውን ጠብቆ ማድረግ፤

ግብ4. ወቅታዊ የፋይናንስ ገቢና ወጪ አፈጻጸም ሪፖርት ይዘጋጃል።

ተግባር 1፡- የ2016 በጀት አመት እቅድ እና በጀት አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት፣

ተግባር 2፡- የሩብ አመት፤የግማሽ አመትና የዓመት የፋይናንስ ሪፖርት ማዘጋጀትና ማቅረብ፣

ተግባር 3፡- በየወሩ የፋይናንስ አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀትና ማቅረብ፣

ተግባር 4፡- የተቋሙን አመታዊ የፋይናንስ ሪፖርት ማዘጋጀት፣

ግብ 5፡-የትብብር መድረኩ ዓመታዊ የሂሳብ ሰነድ ኦዲት ይደረጋል።

ተግባር 1 የድርጅቱን የ2016 ሂሳብ ሰነዶች በውጪ ኦዲተሮች ለማስመርመር ማዘጋጀት፣

ተግባር 2 የድርጅቱን የ2016 በጀት ዓመት የሂሳብ ሰነዶች በውጪ ኦዲተሮች ማስመርመር፣

ተግባር 3 የትብብር መድረኩን የበጀት ዓመት ገቢ እና ወጪ ለቦርድና ለጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ ማጸደቅ፤

ተግባር 4 የ2016 ፀደቀውን ሪፖርትና ኦዲት ሪፖርት ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ እንዲሁም ለአዲት ቦርድ ማስገባት፣

ግብ 6፡- የትብብር መድረኩ አቅም በቢሮ መገልገያዎች እንዲጠናከር ይደረጋል።

ተግባር 1፡- የድርጅቱን እቅድ ለማስፈጸም የሚያገለግሉ የተለያዩ ቋሚ እቃዎች የመለየት ስራ መስራት፣

ተግባር 2፡- የቋሚ እቃዎች ዝቅተኛ መስፈርት (Requirment) በማዘጋጀት የግዢ ሰነድ ማዘጋጀት፣

ተግባር 3፡- የግዢውን ሰነድ ለአቅራቢ ድርጅቶች በመስጠት ፕሮፎርማ መሰብሰብ፣

ተግባር 4፡- በድርጅቱ ህገ ደንብ መሰረት ፕሮፎርማውን በማወዳደር ለአሸናፊው ድርጅት እውቅና መስጠት፣

ተግባር 5፡- ከአሸናፊው ድርጅት ትክክለኛው እቃ እንደሆነ በማረጋገጥ ግዢውን መፈጸም፤

ግብ 7፡- በተቋሙ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶችን የንብረት ማስወገድ ሂደትን ተከትሎ የማስወገድ ስራ ይከናወናል፡፡

ተግባር 1 ንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ በማዋቀር አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶችን መለየት፣

ተግባር 2 ንብረቶቹን ለማስወገድ የሚያስችለውን ዘዴ በመምረጥ ንብረቶቹን በተመረጡ ዘዴዎች ማስወገድ፣

ተግባር 3 የንብረት ማስወገዱን ሂደት ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ ፤

ግብ 8፡- የኢትዮጵያ ከተሞች የትብብር መድረክ አንድ የጠቅላላ ጉባኤና ሁለት የስራ አስፈጻሚ ቦርድ ስብሰባ ይካሄዳል፡፡

ተግባር 1፡-በደብዳቤና በስልክ አባል ከተሞች ጥሪ ማስተላለፍና ክትትል ማድረግ፣

ተግባር 2፡-ለስብሰባው የሚያስፈልጉ የሆቴል አገልግሎት ግዢ በድርጅቱ ህገ ደንብ መሰረት ፕሮፎርማ በመሰብሰብ ለሚያሸንፈው ድርጅት እውቅና በመስጠት ግዥ መፈፀም፣

ተግባር 3፡- ለስብሰባ ለተሳታፊዎች የውሎ አበል፣ የትራንስፖርት እና የሆቴል አገልግሎት ክፍያ መፈጸም፤

ተግባር 4፡- የትብብር መድረኩ ህገ ደንብ በተሻሻለው መመሪያ መሰረት በጠቅላላ ጉባኤ እንዲጸድቅ ይደረጋል፤

ተግባር 5፡- የስራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላት ምርጫ ይካሄዳል፤

ተግባር 6፡- የጠቅላላ ጉባዔውን አፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት፣

ግብ 9፡- የትብብር መድረኩ ሰራተኞችን አቅም ለማጎልበት በስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ መሰረት በተመረጡ የስልጠና ዓይነቶች አንድ የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

ተግባር 1፡- ለድርጅቱ ሠራተኞች አስፈላጊውን የሥልጠና ለመስጠት ፍላጎታቸውን ለመለየት የሚያስችል መጠይቅ ማዘጋጀት፤

ተግባር 2፡- በመጠይቁ መሰረት መስፈርት በማዘጋጀት በአገር ውስጥ የስልጠና ተቋም መምረጥ፤

ተግባር 3፡- ሰልጣኞችን መለየት፤

ተግባር 4፡- በሚወጣው የስልጠና ፕሮግራም መሰረት ስልጠናው እንዲካሄድ ማድረግ፤

ተግባር 5፡- ሰልጣኞች ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማድረግ የስልጠናውን ውጤት መገምገም፤

ግብ 10፡-የትብብር መድረኩን በስራ ላይ የሚገኙ የተቋማዊ ማሻሻያ ጥናት፤ ማኑዋሎችንና መመሪያዎችን የማሻሻል ስራ ይሰራል፣

ተግባር 1፡- የድርጅቱን እቅድ ለማስፈጸም የሚያገለግሉ የተለያዩ ማኑዋሎችና መመሪያዎችን ያሉባቸውን ክፍተቶች የመለየት ስራ መስራት፣

ተግባር 2፡- ለሚሻሻሉት ማኑዋሎችና መመሪያዎች ዝቅተኛ መስፈርት (Requirment) በማዘጋጀት የግገር ሰነድ ማዘጋጀት፣

ተግባር 3፡- ተስማሚውን የግዥ መንገድ መምረጥ

ተግባር 4፡- በተመረጠው የግዥ መንገድ ድርጅቶችን በማወዳደር ለአሸናፊ ድርጅት እውቅና መስጠት፣

ተግባር 5፡- ከአሸናፊው ድርጅት ትክክለኛው አገልግሎት መገኘቱን በማረጋገጥ ክፍያ በመፈጸም ሰነዶቹን መረከብ፤

ክፍል ሶስት፡-

3. የበጀት ዕቅድ፤ መልካም አጋጣሚዎችና ታሳቢ ስጋቶች፤

3.1 የበጀት ዕቅድ

ከሐምሌ 1, 2016 እስከ ሰኔ 30, 2017 የተመደበ በጀት **51,791,684.05** ሲሆን፡-

1.	ከአባል ከተሞች መዋጮ	**40,350,000.00**
	1.1 ውዝፍ ያልተሰበሰበ	11,200,000.00
	1.2 ከነባር አባላት የሚሰበሰብ ዓመታዊ መዋጮ	26,000,000.00
	1.3 ከአዲስ አባላት ምዝገባና አባልነት ክፍያ	3,150,000.00
2.	ከአገር ውስጥ የሚገኝ የፕሮጀክት ድጋፍ	3,000,000.00
3.	ከውጭ የሚገኝ የፕሮጀክት ድጋፍ (ነባር)	1,617,138.56
4.	ከውጭ የሚገኝ የፕሮጀክት ድጋፍ(አዲስ)	5,000,000.00
5.	ከ2016 በባንክ ያለ የዞረ ብር	**1,824,546.05**

ከዚህ ዓመታዊ በጀት ውስጥ ሀያ በመቶው ማለትም 9,670,000 ብር ለመደበኛ ወጪ የተያዘ ሲሆን ቀሪው ሰማኒያ በመቶው ማለትም 42,121,684.05 ደግሞ ለፕሮጀክት ስራዎች የተያዘ እቅድ ነው።

3.2 እቅዱን በመተግበር ሂደት ያሉ መልካም አጋጣሚዎች እና ታሳቢ ስጋቶች

3.1.1 መልካም አጋጣሚዎች

- አዳዲስ የከተማ ልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂዎች እና የህግ ማዕቀፎች መኖራቸው፤
- ለአቅም ግንባታ እና ለልምድ ለውውጥ አጋዥ ከሆኑ ከክልላዊ እና አለምአቀፋዊ የከተሞች እና የአካባቢ መንግስታት ኔትወርኮች ጋር የተጠናከረ ግንኙነቶች መኖሩ።። (UCLGA, UCLG, BRICKS+ Cities, UNDESA, UN Habitat, Cities Alliance, SACN, VNGi, SALGA,)ወዘተ
- በሃገር አቀፍ ደረጃ ለሲቪል ማህበረሰብ ደርጅቶች እንቅስቃሴ ምቹ ሁኔታና ተገቢውን ድጋፍ የሚያደርግ ባለስልጣን መ/ቤት መኖሩ፣

- የትብብር መድረኩ የተሻለ ተቋም ሆኖ እንዲወጣ የሚያግዝ የስራ አመራር ቦርድ መኖሩ፣
- ከከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር እና ከክልል የከተማ ልማት ቢሮዎች ጋር የተፈጠረው መልካምና በትብብር የመስራት ፍላጎትና ልምድ መኖር፣
- አለም አቀፍ ለጋሾች እና የልማት አጋሮች ለአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች እና ለከተማ ልማት ስራዎች ድጋፍ ለማድረግ ፍላጎት ማሳየታቸው፤ ምሳሌ በኢትዮጵያ የአውሮፓ ህብረት (EUD);
- የከተማ አመራሮች የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ በመሆናቸው ልዩ ልዩ ተሞክሮዎችን በዲጂታል ፕላትፎርም ለማካፈል መልካም አጋጣሚ መፍጠሩ፤
- ትብብር መድረኩ ከዩኒቨርሲቲዎች እና ከምርምር ተቋማት ጋር ለምርምርና ስልጠና ተባብሮ ለመስራት ስምምነት መፈራረሙ፤

- የድርጅቱ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ (2015-2019 ዓ.ም) እንዲሁም የተቋማዊ አቅም ዳሰሳ ጥናት (2016 ዓ.ም) የተሰራ መሆኑ፣
- የአባል ከተሞች ዓመታዊ መዋጮ አከፋፈል እየተሻሻለ መሆኑ፣

- በትብብር መድረኩ ዓላማና ጠቀሜታ የሚያምኑና ለእንቅስቃሴውም ድጋፍና እውቅና የሚሰጡ የአባል ከተማ ከንቲባዎችና ሌሎች አመራሮች መኖር ዋና ዋናዎቹ ናቸው፣

3.1.2 ታሳቢ ስጋቶች

- በአገራዊ የሰላምና የጸጥታ ችግሮች ምክንያት ክቡራን ከንቲባዎች በሚዘጋጁ ስልጠናዎች እና ልምድ ልውውጥ መድረኮች በተሟላ ሁኔታ ላይሳተፉ ይችላሉ፡፡
- አመታዊ እቅዱን በብቃት ለመተግበር የፋይናንስ ሃብት ውስንነት ሊያጋጥም ይችላል፡፡
- ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች፤ ለምሳሌ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ንረት፤ (የULGE ፕሮጀክት ከህዳር 30,2017 ጀምሮ ስለሚጠናቀቅ) ፤
- በአንዳንድ ከተሞች የኢንተርኔት ኔትወርክ መቆራረጥ ለስልጠና እና ለልምድ ልውውጥ ጥሪ እና ለኮሙኒኬሽን እክል ሊያጋጥም ይችላል፡፡

- ከአባል ከተሞችና ከለጋሽ ድርጅቶች የሚሰበሰብ ገቢ ወቅቱን ጠብቆ ያለመገኘት፤
- ትብብር መድረኩ በከተሞች ዘንድ የፈጠረው ከፍተኛ መነሳሳት በሃብት እጥርት ምክንያት ፍላጎታቸውን ለማሟላት ውስንነት ሊያጋጥም ይችላል፤
- የደመወዝ ጭማሪ ባለመኖሩ ምክንያት የሰራተኛ ፍልሰት ሊያጋጥም ይችላል፤
- ከተለያዩ አካላት ጋር በቅንጅት የሚፈጸሙ ስራዎች በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት አለመከናወን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፤

ክፍል አራት፡-

4. የዕቅድ ማስፈጸሚያ ስልቶች፤

4.1. የክትትል፣ግምገማ፤ ግብረ መልስና ሪፖርት ሥርዓት

4.1.1 የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት

አቅም ግንባታን በተመለከተ

- የትብብር መድረኩ አባል ከተማ አመራሮችና ባለሙያዎችን የክህሎት እና የእውቀት ክፍተቶችን ለመሙላት በሚዘጋጁ መድረኮች የስልጠና እና የልምድ ልውውጥ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ይከናወናል፡፡

- የተለዩ የአቅም ክፍተቶችን ለመሙላት ለአባል ከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች ስልጠና ይሰጣል፤
- የስልጠና ተሳትፎ ምጣኔ እና የተሳታፊዎች አስተያየትን መነሻ በማድረግ በቀጣይ በሚዘጋጁ ስልጠናዎች እና ልምድ ልውውጥ መድረኮች የእርምት እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡
- ትብብር መድረኩ የሚሰጣቸው የአቅም ግንባታና እውቀት ሽግግር ስራዎች የተጽእኖ ግምገማን መነሻ በማድረግ እቅዶች ይከለሳሉ፤ ለአባል ከተማ ከንቲባዎችና ሌሎች አመራሮች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች እና የሙያ ድጋፎች ይሰጣሉ፡፡
- የትግበራ ሂደቱን በአካል ከመከታተልና ከመደገፍ ባሻገር ስልክ በመደወል የማግባባት ሥራዎች ይሰራሉ፤

ልምድ ልውውጥን በተመለከተ

- የተቀመሩ መልካም ተሞክሮዎች፣ የስልጠና ሰነዶች፣ የዘርፉ የህግ ማዕቀፎች እና ሌሎችም ለአባል ከተሞች ተደራሽ እንዲሆኑ የለማው ድረገጽ በየጊዜው በአዳዲስ ሰነዶች እንዲደራጅ በማድረግ ለአባል ከተሞች ድጋፍ ይደረጋል፡፡
- በአባል ከተሞች መካከል የእውቀት እና የልምድ ልውውጥ መድረኮችን በማመቻቸት የእርስ በእርስ ልምድ ልውውጥ እና ተባብሮ የመስራት ባህል እንዲጎለብት በማድረግ ለከተሞች ድጋፍ ይደረጋል፡፡
- የእውቀት ሽግግር ስርዓት ተገቢነት እና ችግር ፈቺነትን ለማረጋገጥ የተከናወኑ ግምገማዎችን እና ጥናቶችን መሰረት በማድረግ የእውቀት ስራ አመራር የድጋፍ አግባቦች ይሻሻላሉ፡፡
- ለአባል ከተሞች አመራሮችና ባለሙያዎች በልዩ ልዩ ስልጠናዎች እና የልምድ ልውውጥ መድረኮች የተገኙ እውቀቶችን እና ክህሎቶችን ለማጠናከር ቀጣይነት ያለው ሙያዊ ድጋፎች (Coaching & Mentoring) ይሰጣሉ፡፡

- በትብብር መድረኩ ዌብሳይት የቀጥታ ነፃ መረጃ ልውውጥ (free live chat) በኩል ከአባል ከተሞች ለሚነሱ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ሙያዊ ምላሽ እና ማብራሪያ ይሰጣል፡፡
- የተሻሉ ተሞክሮዎች በአባል ከተሞች እንዲተገበሩ እና የትግበራውን ሂደት የመስክ ክትትል በማድረግ በሂደቱም የሚስተዋሉ ችግሮችን በመለየት ለከተሞቹ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል፤
- ተሞክሮዎችን ለማስፋት ቼክ ሊስት በማዘጋጀት በናሙናነት በተመረጡ ከተሞች ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፤ ለከተሞቹም ግብረ-መልስ ይሰጣል፤

4.1.2 የግምገማ፤ ሪፖርትና ግብረ-መልስ ሥርዓት

- በየሳምንቱ መጨረሻ የስራ አፈጻጸም ግምገማ በማድረግ ክፍተቶች ተለይተውና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች እንዲገመገሙ ይደረጋል፤
- በየወሩና በየሩብ አመቱ የዕቅድ አፈፃፀም የመገማገም እና የመገነባባት ሥራ ይሰራል፤ የእርስ በርስ የመማማር ውይይት ይካሄዳል፤
- የስልጠናዎችና አውደጥናቶች ዝክረ ተግባርና አፈጻጸም ሪፖርት በዝርዝር ማዘጋጀት፣
- ለአባል ከተሞች በሚሰጡ ስልጠናዎችና አውደ ጥናቶች ላይ የግብረመልስና ግምገማ እንዲሁም የስልጠናና ልምድ ልውውጥ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ይከናወናል፡፡
- የወር፤የሩብ ዓመት፤የግማሽ ዓመት፤ የዘጠኝ ወርና የአመት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ይዘጋጃል እንዲሁም ይገመገማል፡፡

5. ማጠቃለያ

ይህ ዕቅድ ከወቅቱ ትኩረት አኳያ አዳዲስ ስራዎችን እና የድርጅቱን ስትራቴጂክ እቅድ የትኩረት አቅጣጫዎች መሰረት ተደርጎ ሥራዎችን ለመስራት የተዘጋጀ ሲሆን ዕቅዱን ለማሳካትና አጠቃላይ የትብብር መድረኩን አፈጻጸም ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግን ይጠይቃል። በቀጣዩቹ አመታት የተሻለ ስራ መስራት ይቻል ዘንድ የዚህ እቅድ አፈጻጸም መሰረት በመሆኑ አቅምን አሟጦ መስራት ይጠበቃል። በአፈጻጸም ላይ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ መሻሻል የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች በየጊዜው በመለየት እንዲሻሻሉ በማድረግ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል።

በዕቅዱ ውስጡ የተመለከቱትን ዓላማና ግቦች ለማሳካት የሚያስችሉ ዝርዝር ሥራዎችን ይዟል። ለአፈጻጸሙ የስራ ክፍሎችና የትብብር መድረኩ ባለሙያዎች ሥራቸውን በተናጥል ሳይሆን ቅንጅታዊና የቡድን የአሠራር ዘዴን በመከተልና ከሌሎች የውስጥና የውጭ ተባባሪ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት የላቀ ውጤትን ማስመዝገብ በሚያስችል መንገድ እንዲያከናውኑ ታሳቢ ያደርጋል።